የኮሎምቢያ ዲስትሪክት
የአስተዳደር ጉዳዮች መስሚያ ችሎት ቢሮ የንብረት ማእከል

# በመስሚያ ችሎቱ ላይ ምን ይጠበቃል?

# የOAH ተልዕኮ

የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአስተዳደር ጉዳዮች መስሚያ ችሎት ቢሮ (OAH) የአስተዳደራዊ ፍርድ ቤት ሆኖ ከ 40 በላይ የዲስትሪክት ኤጀንሲዎች፣ ቦርዶች እና ኮሚሽኖች የሚመጡ ተፎካካሪ ጉዳዮች ላይ የሚወስኑ ከ 30 በላይ አስተዳደራዊ ህግ ዳኞች የያዘ ነው። የራስ-ቻል ኤጀንሲው የመስሚያ ችሎቶችን የሚያካሄድ እና ከተለያዩ የኤጀንሲ ውሳኔዎች የሚመጡ ይግባኞች ላይ የሚወስን ገለልተኛ፣ የማያዳላ ፍርድ ቤት ነው። የOAH ዶኬት የሚያካትተው የሥራ-አጥነት ካሳ፣ Medicaid (ሜድክኤድ) እና ሌሎች የህዝብ ጥቅማጥቅሞች፣ ህዝባዊ ቦታ፣ ኪራይ ቁጥጥር፣ የሙያ እና የንግድ ፍቃዶች፣ እና ህንጻ፣ የጤና እና የእሳት-ኮድ ጥሰቶችን የያዙ ጉዳዮችን ነው። OAH በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ህግ ስር የሚነሳ አስተዳደራዊ ክርክርን ለመቆጣጠር እና ለመፍታት ሲባል ለነዋሪዎች ፍትሃዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ሥርዓት በመስጠት በከተማችን ውስጥ የኑሮ ጥራትን ያሻሽላል።

# ከሃላፊነት ማግለል

ይህ በራሪ ጽሑፍ በ የአስተዳደር ጉዳዮች መስሚያ ችሎት ቢሮ (OAH) ውስጥ ስለ መስሚያ ችሎቱ ሂደት የበለጠ እንዲያውቁ እርስዎን ለመርዳት የታሰበ ነው። ይህ መመሪያ የህግ ምክር አይሰጥም። የህግ ምክርን ከህግ ባለሙያ ብቻ ነው ማግኘት የሚችሉት።

የ OAH የንብረት ማእከል እንደዚህ መመሪያ ያሉ የመረጃ ቁሳቁሶችን እያሻሻለ ለማቆየት ይሞክራል፣ ግን ህግ እና ሂደቶች ብዙውን ጊዜ ይለወጣሉ። OAH ለዚህ መረጃ ትክክለኝነት ዋስትና አይሰጥም። በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ ስላለ ማንኛውም ነገር ጥያቄዎች ካሉዎት፣ እባክዎ ለOAH በ (202) 442-9094 ይደውሉ ወይም ለ OAH በ oah.help@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።

በ OAH ያሉ ሁሉም ህገ-ደንቦችን ማየት ከፈለጉ፣ 1 DCMR 28 እና 29 ሚራፎችን ማየት አለብዎት፣ ኦንላይን በ https://oah.dc.gov/page/rules-and-laws ይገኛል።

# የማውጫ ሰንጠረዥ


መግቢያ......4

የመስሚያ ችሎት መጠየቅ......5

ከችሎቱ በፊት......7

የመስሚያ ችሎቱ......9

ከችሎቱ በኋላ......11

# መግቢያ

**የአስተዳደር ጉዳዮች መስሚያ ችሎቶች ቢሮ (OAH) ምንድን ነው?**
OAH ከበርካታ የተለያዩ DC ኤጀንሲዎች የሚመጡ ይግባኞችን የሚሰማ እና የሚወስን በኮሎምቢያ ዲስትሪክት መንግስት ውስጥ ያለ ራሱን-የቻለ ኤጀንሲ ነው። በDC ኤጀንሲ ውሳኔ የማይስማሙ ከሆነ (እንደ ጥቅማጥቅሞች መከልከል፣ የፍቃድ መሻር፣ ወይም የህግ-መጣስ ማሳወቂያ)፣ ወደ OAH ይግባኝ ማለት ይችላሉ። በተጨማሪም እርስዎ ላይ የተላለፈውን ውሳኔ የማይከራከሩ ጊዜ OAH ክፍያዎችን ይቀበላል እና ያስፈጽማል።

**የአስተዳደራዊ ህግ ዳኞች እነማን ናቸው?**
OAH ውስጥ፣ ራስ-ቻል አስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ ስለ ጉዳዮ ምስክርን ይሰማል እና ውሳኔ ይሰጣል። ዳኞቹ የመጀመሪያ ውሳኔ ላስተላለፈው ኤጀንሲ አይሰሩም። ዳኞቹ ራሱን በቻለ ኮሚሽን ይሾማሉ። OAH ዳኞች በዙ የስራ ዓመታትን ያሳለፉ ልምድ ያላቸው የህግ ባለሙያዎች ናቸው እና ከብዙ የተለያዩ የህግ ኋላ-ልምዶች የመጡ ናቸው። የእያንዳንዱ ዳኛ የህይወት ታሪኮች በ https://oah.dc.gov/page/alj-biographies ይገኛሉ።

**የመስሚያ ችሎት ምንድን ነው?**
በ OAH የሚደረገው የመስሚያ ችሎት ከፍርድ ችሎት ጋር ይመሳሰላል። ዳኛ የመስሚያ ችሎቱን ይቆጣጠራል እና እያንዳንዱ ጎራ ማስረጃ እና የምስክርነት ቃልን እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣቸዋል። የመስሚያ ችሎቶች እንደ ህግ ችሎት ያህል መደበኛ ባይሆኑም፣ ዳኛው የሚተገበራቸው የ OAH ህገ-ደንቦች አሉ። ከኤፕሪል 1, 2020 ጀምሮ፣ ዳኞች በተጨማሪ የCOVID-19/ኮሮናቫይረስ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ህጎችን ለጊዜያዊነት ይተገበራሉ፣ የOAH የርቀት አሰራር ሁኔታን ለመግለጽ በርካታ የ OAH ህገ-ደንቦችን የሚያሻሽል። የOAH ህጎች እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ህጎች በ https://oah.dc.gov/page/rules-and-laws ይገኛሉ።

**አስተርጓሚ ማግኘት እችላለሁ?**
ከኢንግሊዝኛ የተለየ ቋንቋ የሚናገሩ ከሆነ እና አስተርጓሚ ካስፈለገዎ፣ OAH በነፃ አንድ ያቀርባል። እባክዎ በተቻለ ፍጥነት ለOAH ይንገሩ። አስተርጓሚ ስለመፈለገዎ እርግጠኛ ካልሆኑ፣ እባክዎ ለማንኛውም ነገር አንድ እንመጣልዎ ይጠይቁ። ጓደኛ፣ የቤተሰብ አባል፣ ወይም በጉዳዩ ውስጥ ያለ ሌላ አካል እንዲተርጎምልዎ ማድረግ አይችሉም። ለአስተርጓሚ ለመጠየቅ፣ እባክዎ ለOAH በ (202) 442-9094 ይደውሉ ወይም ለOAH በoah.filing@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።

# የመስሚያ ችሎት መጠየቅ

**OAH ጉዳየን እንዲሰማ እንዴት እጠይቃለሁ?**
ለመስሚያ ችሎት በጽሁፍ መጠየቅ አለብዎት። የጽሁፍ ጥያቄዎ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፥

(a) የክርክርዎ አጭር መግለጫ፤
(b) ዳኛው ምን እንዲያደርግልዎ እንደሚፈልጉ፤
(c) ቀኖች እና ሌሎች አስፈላጊ እውነታዎች፤
(d) ይግባኝ እየጠየቁበት ያሉዎት የውሳኔው ቅጂ፤ እና
(e) ሙሉ ስምዎ እና የግንኙነት መረጃ።

ለተወሰኑ የጉዳይ ዓይነቶች፣ የመስሚያ ችሎት ለመጠየቅ ሞልተው በኢሜይል፣ ፖስታ፣ ወይም ፋክስ ለOAH መላክ የሚችሉትን የናሙና ቅጾችን OAH ያቀርባል። ቅርጾቹ በ https://oah.dc.gov/page/filings-and-forms ይገኛሉ።

በCOVID-19/ኮሮናቫይረስ የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት፣ OAH ለበ-አካል ጉብኝቶች ወይም በአካል መሙላቶች ክፍት አይሆንም። ባሁን ጊዜ OAH በኢሜይል፣ ፖስታ፣ እና ፋክስ ለመጠየቅ የሚገቡ ሰነዶችን ብቻ ይቀበላል፥

- ኢሜይል፥ oah.filing@dc.gov
- ደብዳቤ፥ 441 Fourth Street, NW, Suite 450 North
  Washington፣ DC 20001
- ፋክስ፣ (202) 442-4789

የመስሚያ ችሎት ስለመጠየቅ ማንኛውም ጥያቄዎች ካሉዎት፣ ለOAH በ (202) 442-9094 ይደውሉ።

**ቀጥሎ ምን ይፈጠራል?**
የመስሚያ ችሎት ከጠየቁ በኋላ፣ OAH እርስዎ በሰጧቸው አድራሻ **የቀጠሮ ሰሌዳ ትዕዛዝን** በፖስታ ይልካሉ። ለOAH የኢሜይል አድራሻ ከሰጡ፣ OAH በተጨማሪም የቀጠሮ ሰሌዳ ትዕዛዝን በኢሜይል ይልካል። **ማስታወሻ፥ ከ** OAH ለሚላኩልዎ ኢሜይሎች የጃንክ ወይም የስፓስም ኢሜይል ሳጥንዎን ያረጋግጡ።

**የቀጠሮ ሰሌዳ ወረቀየመስሚያ ችሎትዎ ቀን እና ሰዓት እና ችሎቱ ምን እንደሚሸፍን የሚነግርዎ ከፍርድ ቤት የሚላክ የጽሁፍ ትዕዛዝ ነው። ማስታወሻ፣** በአንድ አንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ ውሳኔውን ይግባኝ እያሉ ያሉ ኤጀንሲ በ OAH የመስሚያ ችሎት ማግኘት ከመቻልዎ በፊት አስተዳደራዊ ግምገማ ሊያደርግ ይችላል። አስተዳደራዊ ግምገማ ማለት ከችሎቱ በፊት ጉዳዩን ለመፍታት እርስዎ እና የተቃራኒ አካል (ወይም ኤጀንሲ) መሀል የሚደረግ ስብሰባ ነው።

በCOVID-19/ኮሮናቫይረስ የህዝብ ጤና አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት OAH በርቀት ስለሚሰራ የእርስዎ የቀጠሮ ሰሌዳ ትዕዛዝ የርቀት ችሎትዎን በስልክ እንዴት እንደሚሳተፉ ላይ መመሪያዎች ይኖሩታል።

### የርቀት ችሎት እንዴት ይሰራል?

OAH የርቀት የመስሚያ ችሎቶችን ለማካሄድ እና ለመመዝገብ WebEx የምባለው የኮምፒውተር ፕሮግራምን ይጠቀማል። የርቀት የመስሚያ ችሎትዎን ለመሳተፍ የሚያስፈልገዎት ብቸኛው ነገር ስልክዎ ነው። የእርስዎ የቀጠሮ ሰሌዳ ትዕዛዝ የስልክ ቁጥር፣ የማግኛ ኮድ፣ እና ለችሎትዎ ላይ እንዴት እንደሚደውሉ ላይ መመሪያዎች አሉት።

### የርቀት የመስሚያ ችሎቴን መሳተፍ አለብኝ?

አዎ። የርቀት የመስሚያ ችሎት ላይ መሳተፍ **አለብዎት።** ካላደረጉ፣ በጉዳዮ ሊሸነፉ ይችላሉ።

የመስሚያ ችሎትን ለበቂ ምክንያት ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ካለብዎት (እንደ እንዳይገኙ የሚከለክልዎ የህክምና ሁኔታ፣ ሌላ ፍርድ ቤት እንዲገኙ ቀጠሮ ካለዎት፣ የልጅ-እንክብካቤ ጉዳይ ካለዎት፣ ከሥራዎ ከቀሩ ሥራዎ ችግር ውስጥ የሚገባ ከሆነ፣ ወዘተ. ያሉ)፣ የጽሁፍ **ለሌላ የመስሚያ ችሎት ቀነ-ቀጠሮ መጠየቅ** (እንዲሁም **የቀጣይነት ረቂቅ** ተብሎ የሚታወቀው) ማመልከቻ በማስገባት ለሌላ የመስሚያ ችሎት ቀነ-ቀጠሮ መጠየቅ ይችላሉ። ስለ ተቃርኖው እንዳወቀዉ **በተቻለ ፍጥነት** ለሌላ የመስሚያ ችሎት ቀነ-ቀጠሮ መጠየቅ አለብዎት። OAH በተለምዶ አስቸኳይ-ላልሆኑ የግል ምክኒያቶች ወይም የንግድ ቀጠሮዎች ሲል የመስሚያ ችሎትን ወደ ሌላ ጊዜ አያሳልፍም። እንዲሁም ዳኞች ብዙ ጊዜ ለተለየ የመስሚያ ችሎት ቀነ-ቀጠሮ የመጨረሻ-ደቂቃ ጥያቄን አይቀበሉም፣ እንደ ህክምና ድንገተኛ ሁኔታ ያለ፣ ያልታሰበበት፣ ከቁጥጥርዎ ውጭ የሆነ ከባድ ግጭት ካለዎት በስተቀር።

ጥያቄዎን ስላስገቡ ብቻ ጥያቄዎ ተቀባይነት እንዳገኘ **አያስቡ።** ቀኑን ከሚቀይር ዳኛ የጽሁፍ ትዕዛዝ ከደረሰዎት በስተቀር እንደ ቀጠሮው ወደ ችሎቱ መምጣት ይኖርብዎታል።

### የጽሁፍ ጥያቄን (እንዲሁም ረቂቅ ተብሎ የሚታወቀው) OAH ጋ እንዴት ማስገባት እችላለሁ?

ለተለየ የመስሚያ ችሎት ቀነ-ቀጠሮ ጥያቄ ወይም ሌላ ማንኛውም የጽሁፍ ጥያቄ ከማስገባትዎ በፊት፣ ሌላኛውን አካል ለማግኘት መሞከር እና ለስምምነት መጠየቅ አለብዎት። በጥያቄዎ ውስጥ ለማግኘት እንደሞከሩ እና ሌላኛው አካል ተስማምቶ እንደሆነ መናገር አለብዎት። እንዲሁም የጥያቄዎን ቅጂ በጉዳዮ ውስጥ ላሉ ሌሎች ሁሉም አካላት ሁል ጊዜ መላክ አለብዎት።

ጥያቄውን ለ OAH በኢሜይል፣ ፖስታ፣ ወይም ፋክስ ወደ OAH በመላክ መጠየቅ ይኖርብዎታል (ለ OAH የግንኙነት መረጃ የዚህን በራሪ ወረቀት ገጽ 5 ይመልከቱ)።

ለተወሰኑ የጥያቄ ዓይነቶች (ለተለየ የመስሚያ ችሎት ቀነ-ቀጠሮ ጥያቄን ጨምሮ)፣ እርስዎ ሞልተው ለ OAH መላክ የሚችሏቸው የአብነት ቅጾችን OAH ያቀርባል። ቅጾቹ በ https://oah.dc.gov/page/filings-and-forms ይገኛሉ።

**በመስሚያ ችሎቱ ምን ይፈጠራል?**
ሌሎች የመስሚያ ችሎቶች ዓይነቶች አሉ። አንድ አንድ ጊዜ፣ባለጉዳዮቹ ጉዳዮች ምን እንደሆኑ ለዳኛው መናገር፣ ወደ መስማማት መሄድ ይቻል እንደሆነ ለመወሰን፣ ወይም ረዘም-ላለ የመስሚያ ችሎት የሚገኙበት ጊዜን ለዳኛው ለመናገር እንዲችሉ ዳኛ የቅድሚያ የመስሚያ ችሎትን ይቀጥራል። በሌሎች ጊዜያት፣ ዳኛው ወዲያውኑ የማስረጃ ማቅረቢያ ችሎትን ያዋቅራል። ለምን ዓይነት ችሎት እንደተቀጠሩ ለመረዳት የተቀበሉትን ትዕዛዝ በጥንቃቄ ማንበብዎን እርግጠኛ ይሁኑ። እርግጠኛ ካልሆኑ፣ ለመጠየቅ OAH ያግኙ።

**የማስረጃ ማቅረቢያ ችሎት** ሁሉም አካላት በራሳቸው በኩል ያለውን ታሪክ ለዳኛው እንዲናገሩ እድል ይሰጣል። የእርስዎን ታሪክ/እውነታ ለመናገር፣ እርስዎ መመስከር እና ምስክሮች እንዲመሰክሩልዎት ሊያደርጉ ይችላሉ። እንዲሁም ዳኛው ሰነዶችን፣ ፎቶዎችን፣ ወይም ሌላ አካላዊ ማስረጃ እንዲመለከት ሊጠይቁ ይችላሉ። እንዲሁም የሌላኛው አካል ማስረጃን ይሰማሉ እና የሌላኛው አካል ምስክሮችን የመጠየቅ እድል ይኖረዎታል። ዳኛው የችሎቱ ሂደትን እንደተረዱ እና ጉዳዮን ለማቅረብ የሚፈልጉትን ጊዜ እንዲያገኙ ያረጋግጣል።

# ከችሎቱ በፊት

**የህግ-ጠበቃ ያስፈልገኛል?**
በችሎቱ ላይ የህግ-ባለሙያ እንዲኖረዎት ይፈቀዳል፣ ግን አንድ እንዲኖረዎት አይኖርቦትም። በአንድ አንድ የጉዳዮች ዓይነቶች ውስጥ፣ የህግ-ጠበቃ ከሌሎት፣ የህግ-ባለሙያ ያልሆነ ተወካይን ይዘው ሊመጡ ይችላሉ። እርግጠኛ ካልሆኑ፣ OAH ያግኙ።

የህግ-ጠበቃ ወይም ተወካይ ካስፈለገዎት፣ ለዚያ ሰው በተቻለ መጠን ስለ የመስሚያ ችሎቱ ቀነ-ቀጠሮ መናገር አለብዎት። የህግ-ጠበቃ ማግኘት የማይችሉ ከሆነ፣ ግን አንድ የሚፈልጉ ከሆነ፣ የ OAH የንብረት ማእከልን በስልክ በ (202) 442-9094 ወይም በኢሜይል በoah.help@dc.gov ማግኘት ይችላሉ። እርስዎን እንዲወክል ጠበቃ እንደሚያገኙ OAH ዋስትና መስጠት አይችልም፣ ግን OAH በነፃ ወይም በቅናሽ ዋጋ ሊወክሉዎ የሚችሉ የድርጅቶች ዝርዝር አለው፤ እና፣ በአንድ አንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ የንብረት ማእከሉ እርስዎን ከህግ-ጠበቃ ጋር ለማገናኘት ሊረዳ ይችላል።

በችሎቱ ላይ እርስዎ ራስዎን ሊወክሉ ይችላሉ (በተጨማሪም የራስ ውክልና ተብሎ ይታወቃል) እና የህግ-ጠበቃ ወይም ተወካይ እንዲኖረዎት አያስፈልግዎትም።

**በእርስዎ በኩል ያለውን ታሪክ ለመናገር ይለማመዱ።**
የእርስዎ ምስክርነት ዓላማ እውነታዎችን ለዳኛ መናገር ነው፣ እንጂ በቀጥታ ከሌላኛው አካል ጋር ለመከራከር አይደለም። የእርስዎን ምስክርነት የጉዳዮን እውነታዎች እንደሚናገር ንግግር አድርገው ያስቡት። ተራዎ ሲሆን፣ ዳኛው በእርስዎ በኩል ያለውን የጉዳይ ጎን እንዲናገሩ ይፈቅድልዎታል።

በጉዳይ ውስጥ እራስዎን እየወከሉ ከሆነ፣ በተጨማሪም፣ ለምን ማሸነፍ እንዳለብዎ ጉዳዮን እና ክርክርዎን ለማጠቃለል የመክፈቻ ንግግር እና የመዝጊያ ክርክር ሊያዘጋጁ ይችላሉ።

**ምስክሮችን ማምጣት እችላለሁ?**
ስለ ጉዳዮቹ ሌሎች ሰዎች ማስረጃ ካላቸው፣ ወደ ርቀት መስሚያ ችሎት እንዲሄዱ እና እንዲመሰክሩ ሊጠይቋቸው ይችላሉ። ምስክሮችዎ የርቀት ችሎቱን እንዲቀላቀሉ የመግባት-መጥሪያ መረጃ ሊሰጧቸው ይገባል። ምስክሮቹ ችሎቱ ላይ ለመሳተፍ ፍቃደኛ ካልሆኑ፣ **ለፍርድ ቤት መጥሪያ** ለማመልከት ጥያቄ ሊያስገቡ ይችላሉ። የፍርድ ቤት መጥሪያ ምስክሩ መጥቶ እንዲመሰክር የሚያደርግ ትዕዛዝ ነው። እንዲሁም ምስክሩ ሰነዶችን እንዲያመጣ ለማስደረግ ለፍርድ ቤት መጥሪያ መጠየቅ ይችላሉ። ዳኛ የፍርድ ቤት መጥሪያ ወረቀት ያዝ እንደሆነ ይወስናል። ዳኛው የመጥሪያ ወረቀቱ ላይ ከፈረመ፣ እርስዎ ወይም ጓደኛዎ ወረቀቱን ለምስክሩ/መስካሪው መስጠት አለባችሁ።

በኪራይ መኖሪያ ቤቶች እና የሥራ-አጥነት መድን ጉዳዮች ውስጥ፣ ዳኛው እንዲያጸድቃቸው ሳይጠይቁ እስከ ሦስት የፍርድ ቤት መጥሪያ ወረቀቶችን ከጸፊ ቢሮ ሊቀበሉ ይችላሉ።

**ሰነዶችን ወይም ሌላ ማስረጃን መላክ እችላለሁ?**
ጉዳዮን እንዲያሸንፉ የሚረዱዎ የጽሁፍ ሰነዶች፣ ፎቶግራፎች፣ ቪድዮዎች፣ ወይም ሌሎች ቁሳቁሶች ካሉዎት፣ ዳኛው በችሎቱ ወቅት እንዲያያቸው እና የጉዳዩ መደበኛ መዝገብ አካል ለማድረግ ሊጠይቁ ይችላሉ። በተጨማሪም ዳኛው የድርጊቱን ቅጂ እንዲያይ ወይም እንዲሰማ ሊጠይቁ ይችላሉ።

እርስዎ ለማስረጃ ሊጠቀሙባቸው የፈለጉ ፎቶግራፎች የሚያሳየውን ሁኔታ በፍትሃዊነት እና በትክክል መወከል አለበት። **ማስታወሻ፥** እርስዎ መጠቀም የፈለጉ የዲጂታል ፎቶዎች ወይም ቪድዮዎች በካሜራ ወይም ስልክ ላይ ካሉዎት፣ ቅጂያቸውን ለዳኛ እና ለሌሎች አካላት መላክ እንዲችሉ ፎቶዎችን ማውረድ ወይም ማሳተም እና ቪድዮዎችን ማውረድ አለብዎት። በችሎቱ ወቅት ፎቶዎችን ወይም ቪዲዮዎችን በካሜራዎ ወይም ስልክዎ ውስጥ ብቻ ከያዙ፣ ፎቶዎቹ ወይም ቪዲዮዎቹ መዝገብ ላይ ሊጨመሩ አይችሉም፣ ስለዚህ ዳኛው በጉዳዮ ላይ ውሳኔ በሚያስተላልፍበት ወቅት ጥቅም ላይ ሊውሉ አይችሉም።

**የማስረጃ እና ምስክር ዝርዝርዎን ለሌላኛው አካል ይስጡ።**
በጊዜ ሰሌዳ ትዕዛዝዎ ውስጥ ያሉ መመሪያዎችን መከተል አለብዎት። ከችሎቱ **በፊት** የማስረጃዎን ቅጂ ለሌላኛው አካል እና ለOAH ይላኩ። ሁለቱም አካላት ከችሎቱ በፊት የማስረጃ እና ምስክር ዝርዝሮቻቸውን ማጋራት አለባቸው። ይህ በችሎቱ ወቅት ማንም እንዳይገረም ያረጋግጣል። ዳኛው ከችሎቱ በፊት ለሌላኛው አካል ያላሳዩትን ማንኛውም ማስረጃ እንዲጨምሩ ላይፈቅድልዎት ይችላል።

# የመስሚያ ችሎቱ

**የርቀት መስሚያ ችሎቱን አስቀድመው ለመቀላቀል ያቅዱ።**
ዳኞቹ ችሎቱን በጊዜ ያስጀምራሉ። ከዘገዩ፣ ችሎቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ያልፍዎታል። ችሎትዎ ካለፈዎት፣ ወዲያውኑ በጉዳዮ ላይ ሊሸነፉ ይችላሉ።

ቁጥሩ እና የተደራሽነት ኮድ እንዲሰራ ለማረጋገጥ የርቀት ችሎቱን የተወሰኑ ደቂቃዎችን አስቀድመው ይቀላቀሉ። ችሎቱን እንዳይቀላቀሉ የከለከሉዎ የቴክኒክ ችግሮች ካሉዎት፣ ወዲያውኑ (202) 442-9094 ላይ ይደውሉ። የቴክኒክ ጉዳዩን ለመፍታት የ OAH ሠራተኛን በስልክ ማግኘት ባለመቻልዎ ችሎቱ ካለፈዎ፣ ጉዳዩን ለማብራራት እና ሌላ የመስሚያ ችሎት ቀን ለመጠየቅ በተቻለ ፍጥነት ለOAH ይደውሉ ወይም ኢሜይል ይላኩ።

**ዳኛው ለምን የWebEx ችሎትን ይቀዳል?**
የችሎቱ የዲጂታል ቅጂ በችሎቱ ወቅት የሆነውን ነገር **ይፋዊ ቅጂ** ነው። የOAH የመስሚያ ችሎት ሲጀምር፣ ዳኛው ጉዳዩን ይፋ ያደርግ እና ጉዳዩ በ OAH እንዴት እንደተጀመረ ሊያወራ ይችላል። ዳኛው ለቅጂው ሲባል አካላቱ ስሞቻቸውን እንዲገልጹ ይጠይቃል። ይህ የሚሆነው በኋላ የተዘጋጀው ማንኛውም የተጻፈ ጽሁፍ ማን እየተናገረ እንዳለ በትክክል እንዲገልጽ ነው።

**የጉዳይ ይፋዊ ቅጂ** የሚጨምረው ከዳኛው የተጻፉ ትዕዛዛት፣ በባለጉዳዮቹ የተሰጠ ሁሉም ማስረጃ፣ እና የመስሚያ ችሎቱ ቅጂን ነው። በጉዳዩ ውስጥ የOAH ውሳኔ ይግባኝ ከተባለ፣ ይፋዊ ቅጂ ይግባኝ እየተባለ ጉዳይን ለሚሰማ እና ለሚወስን ዳኛ ወይም የውሳኔ ሰጪ ይላካል።

እንዲሁም የተቀዳ ችሎቱን ቅጂ በ $10 የማስኬጃ ዋጋ ማግኘት ይችላሉ። ቅጂ ለማግኘት፣ **የመስሚያ ችሎት የድምጽ ቅጂ መጠየቂያን፣** በ $10 ክፍያ ዋጋ ጋር፣ለ OAH ይላኩ። ለጥያቄው የአብነት ቅጽ በ [https://oah.dc.gov/page/filings-and-forms](https://oah.dc.gov/page/filings-and-forms) ይገኛል።

**ችሎቱ እንዴት ይካሄዳል?**
በእርሱ በኩል ያለውን ነገር ማረጋገጥ ያለበት አካል/ባለጉዳይ (የማረጋገጫ ጫና ይባላል) ብዙውን ጊዜ ይጀምራል። ያ ባለጉዳይ የእሱ/ሷን ሙሉ ጉዳይ መጀመሪያ ያቀርባል—ሁሉም ምስክሮች እና የሰነድ ማስረጃ። ለዚህ የተወሰኑ ልዩ አይታዎች አሉ። ለምሳሌ፣ አንድ አንድ ጊዜ ኤጀንሲ ጥቅማጥቅሞችን ለአንድ ሰው ለምን እንደከለከለ የበለጠ መረጃ አለው፣ ምንም እንኳ ጠያቂው (ጥቅማጥቅሞች ይገባኛል ጥያቄ አቅራቢ) ለጥቅማጥቅሞች ብቁ መሆኑን የማሳየት ጫና ቢኖርበትም። በእነዚህ ጉዳዮች ውስጥ፣ ኤጀንሲው ብዙ ጊዜ ጉዳዩን መጀመሪያ ያቀርባል።

ዳኛው ማንኛውም ምስክሮች እንዲምሉ ያደርግ፣ እና ከዚያ ምስክሮቹ የሚያውቁትን ነገር ይናገራሉ። የህግ-ጠበቃ ከሌሎት፣ ዝም ብለው ታሪክዎን መናገር ይችላሉ። ጠበቃ ወይም ተወካይ ካለዎት፣ ያ ሰው ጥያቄዎችን ይጠይቆታል። ምስክሮችን ይዘው ከመጡ፣ ጥያቄዎችን ሊጠይቋቸው ይችላሉ። በተጨማሪም ዳኛው ለእርስዎ ወይም ለምስክሮችዎ ጥያቄዎች ሊኖሩት ይችላሉ።

እያንዳንዱ ምስክር ከሄደ በኋላ፣ ሌላኛው ባለጉዳይ/አካል ያንን ምስክር ሰጪ የመስቀለኛ ጥያቄን መጠየቅ ይችላል። የመስቀለኛ ምርመራ የመስካሪውን ምስክርነት የሚፈታተኑ ወይም ተጨማሪ ማብራርያ የሚያሰጡ ጥያቄዎችን እንዲጠይቁ ያደርጋል። የመስቀለኛ ምርመራ ከሌላኛው አካል ጋር እንዲከራከሩ ወይም የራስዎን ምስክርነት እንዲሰጡ እድል **አይሰጥም።**

እርስዎ ምስክርነት ሲሰጡ፣ ዳኛው ሰነዶችዎን እንዲመለከት እና የጉዳዩ ይፋዊ መዝገብ ውስጥ "እንዲያስገባ" ሊጠይቁት ይችላሉ። ዳኛው ሰነዶቹ እውነተኛ እና ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይኖርበታል። እንዲሁም ዳኛው ለሌላኛው አካል የሰነዱን ማስገባት የመቃወም እድል መስጠት ይኖርበታል።

ችሎቶችን እና ማስረጃን የሚያስተዳድሩ ህጎች በOAH ህጎች ውስጥ አሉ፣ በ https://oah.dc.gov/page/rules-and-laws ይገኛሉ። በ OAH ውስጥ የሚደረግ ችሎት ውስጥ፣ የማስረጃ ህጎች በሌሎች ፍርድ ቤቶች እንዳሉ ጠንካራ ላይሆኑ ይችላሉ። የማስረጃ ህጎች የችሎቱ ሂደት ለሁሉም አካላት ፍትሃዊ እንደሆነ ለማረጋገጥ የተዘጋጁ ናቸው።

**በችሎቱ ጊዜ ጥያቄ ቢኖረኝስ ምን አደርጋለሁ?**
የሆነ ነገር የማይረዱ ከሆነ፣ ዳኛው እንዲያብራራ ይጠይቁት። አንድ አንድ ባለጉዳዮች የህግ-ባለሙያ እንዳልሆኑ ዳኞች ያውቃሉ፣ እና ጥያቄዎችን መመለስን ለምደዋል። ነገር ግን ዳኛው በጉዳዮ ላይ ምክር ሊሰጥዎት ወይም ማስረጃዎን እንዲያቀርቡ ሊረዳዎት እንደማይችል ሁል ጊዜ ያስታውሱ።

# ከችሎቱ በኋላ

**የችሎቱን ውጤት እንዴት ማወቅ እችላለሁ?**
ዳኛው ምናልባት እራሱ ችሎቱ ላይ ውሳኔ አይሰጥም ይሆናል። ከችሎቱ በኋላ፣ ዳኛው የመጨረሻ ትእዛዝን ከዳኛው ውሳኔ ጋር ይጽፋል። OAH የመጨረሻ ትእዛዝን ለእርስዎ እና በጉዳዩ ውስጥ የተሳተፉ ለሌሎች አካላት በፖስታ ወይም በኢሜይል ይልካል። **ማስታወሻ፥ እባክዎ የጀንክ ወይም ስፓስም ኢሜይል ሳጥንዎን ይመልከቱ።**

**በመጨረሻ ትእዛዝ ካልተስማማሁ ምን ማድረግ እችላለሁ?**
በመጨረሻ ትዕዛዝ ውስጥ ባለው ውጤት ካልተስማሙ፣ ብዙ ጊዜ ከሁለት ነገሮች አንዱን ማድረግ ይችላሉ። መጀመሪያ፣ ከOAH ጋር **መልሶ የማየት ረቂቅ** ማስገባት ይችሉ ይሆናል፣ ዳኛው የመጨረሻ ትእዛዙን እንዲቀይር ወይም ሌላ ችሎትን እንዲቀጥር በመጠየቅ። ሁለተኛ፣ በኮሎምቢያ ዲስትሪክት የይግባኞች ፍርድ ቤት ጋር (ወይም ሌላ የይግባኝ አካል ጋር፣ ጉዳዩ ላይ በመመስረት) ይግባኝ ሊያስገቡ ይችላሉ። የመጨረሻ ትእዛዝዎን በጥንቃቄ ያንብቡ ምክንያቱም እያንዳንዱ የመጨረሻ ትእዛዝ የት እና እንዴት ይግባኝ እንደሚጠይቅ መግለጫ ስላለው። ብዙውን ይግባኞችን ለማስገባት ጥብቅ የመጨረሻ ቀነ-ገደቦች አሉ። ሌላ የOAH መመሪያ "የመጨረሻ ትእዛዝን መረዳት" የተባለው (በ https://oah.dc.gov/service/oah-resource-center ይገኛል) ተጨማሪ መረጃ ሊሰጥዎ ይችላል።

**ከችሎቱ ምን እንደሚጠብቁ ተጨማሪ ጥያቄው ካሉዎት ወይም በዚህ በራሪ ወረቀት ውስጥ ስላለው ማንኛውም ነገር ተጨማሪ ማብራሪያ ከፈለጉ፣ እባክዎ ለOAH በ (202) 442-9094 ይደውሉ ወይም ለOAH በ oah.help@dc.gov ኢሜይል ይላኩ።**

# ማስታወሻዎች




የኮሎምቢያ ዲስትሪክት የአስተዳደር ችሎቶች ቢሮ

One Judiciary Square

441 4th Street, N.W., 570N

Washington፣ DC 20001

ስልክ ቁጥር፥ 202-442-9094

ፋክስ፥ 202-442-4789

http://oah.dc.gov